# የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር

## ውሎና አዳራቸውን ጎዳና ላይ ያደረጉ ሕፃናት እና እናቶች ከህፃን ልጆቻቸው ጋር መልሶ ማቋቋምን በተመለከተ በክዋኔ ኦዲት ለተሰጡ አስተያየቶች የቀረቡ ግብረ-መልሶች

ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግስት ወጪ አስተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የቀረበ

ታህሳስ 12/ 2015

# በክዋኔ ኦዲቱ ሪፖርት የተጠቀሱት የኦዲት ግኝቶችን ለማረም የተወሰዱ እርማጃዎች

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በተሰጠው አስተያየት መሠረት የማሻሻያ ሃሣቦች አተገባበር መርሐ-ግብርን በማዘጋጀት በቀን የካቲት 29/2014 ዓ.ም ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤቱ እንዲላክ አድርጓል፡፡

# በክዋኔ ኦዲት የተሰጡ ማሻሻያ ሃሣቦች

1) ሚኒስቴር መ/ቤቱ ውሎና አዳራቸውን ጎዳና ላይ ያደረጉ ሕፃናት እና እናቶች ከሕፃን ልጆቻቸው ጋር ውሎና አዳራቸውን ጎዳና ላይ እንዳያደርጉ ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል እንዲሁም መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር በመተባበር ጎዳና ላይ የሚወጡ ዜጎችን መከላከል ወይም ቁጥሩ እንዲቀንስ ለማድረግ የሚያስችል የጋራ ዕቅድ ሊያቅድ እና ተግባራዊ በማድረግ አፈጻጸሙን በየጊዜው የሚገመገምበት የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

# በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተወሰዱ/በመወሰድ ላይ ያሉ የማስተካከያ እርምጃዎች

- ሚ/ር መስሪያ ቤቱና በተዋረድ ያሉ ተቋማት ሕፃናት እና እናቶች ከሕፃን ልጆቻቸው ጋር ወደ ጎዳና እንዳይወጡ ለመከላከል ስራዎችን ተባብሮ ለመስራት የሚያስችል የ2015 የበጀት ዓመት ዕቅድ ተዘጋጅቶ በጋራ በመፈራርም ወደ ስራ ገብቷል፡፡ Image
- ሚ/ር መስሪያ ቤቱ ከዓለም ባንክ በተገኘው የገንዘብ ድጋፍ በመጀመሪያ የፕሮጀክቱ ምዕራፍ 22,000 ለማንሳት ታቅዶ 20,991 ወደ ጎዳና የወጡትን ዜጎችን ከጎዳና በማንሳት በአገልግሎት ሰጪ ተቋማት የተለያዩ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ከተደረገ በኃላ ወደ መጡበት ማህበረሰብና ቤተሰብ እንዲመለሱ በማድረግ የማቋቋም ሥራ ተከናውነዋል፡፡ የስራዉ አፈጻጸምም ውጤታማ እንዲሆን በየጊዜው የሚመለከታቸውን አካላት በማሳተፍ እንዲገመገም ተደርጓል፡፡ በዚህም 6598 ሕፃናት እና 6167 ሕፃናት የያዙ እናቶች ፤4114 አረጋዊያንና 4112 አዋቂዎችን ማቋቋም ተችሏል፡፡

# የቀጠለ-------------

በሁለተኛው  የፕሮጄክቱ ምዕራፍም  22,000  ዜጎችን ከጎዳና በማንሳት መልሶ ለማቋቋም ሚ/ር መስሪያ  ቤቱ ከአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ጋር ውል ለመፈራረም በሂደት ላይ ይገኛል፡፡

በተጨማሪም ከሚመለከታቸው የመንግስትና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተበባር አገራዊ የንቅንቄ መድረክ በመፈጠር ዜጎች ወደጎዳና እንዳይወጡ ለማድረግ ስራዎች በመሰራት ላይ ይገኛል፡፡

# በክዋኔ ኦዲት የተሰጡ ማሻሻያ ሃሣቦች

2) እናቶችን በማዕከላት ቆይታቸው የሚሰጣቸውን ሥልጠና አጠናቀው ወደ ስራ ለመግባት ፍላጎት ያላቸውን ማንነታቸውን የሚገልፅ መታወቂያ እንዲያገኙ ከሚመለከታቸው የክልል እና የከተማ አስተዳደር አካላት ጋር በመነጋገር መፍትሄ እንዲያገኙ እና ዳግመኛ ወደ ጎዳና እንዳይወጡ ያለውን ሁኔታ የሚቀነስበትን መንገድ ሊፈልግ ይገባል፡፡

# በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተወሰዱ/በመወሰድ ላይ ያሉ የማስተካከያ እርምጃዎች...

- የማዕከላት ቆይታቸውን አጠናቀው የተቋቋሙ እናቶች በመታወቂያ እጦትና በክትትል ማነስ ተመልሰው ወደ ጎዳና እንዳይወጡ ተቋቋሚ እናቶችን የሚከታተሉት የአገልግሎት ሰጪ ተቋማትና በታችኛው እርከን የሚገኙት የመንግስት አስፈጻሚ ተቋማት ተናበው በመስራት መታወቂያ የሚያገኙበት ሁኔታ እንዲያመቻቹ መግባባት ላይ ተደረሶ ስራዎች በዚሁ አግባበብ በመፈጸም ላይ እያለ ከወቅታዊ የሰላምና ፀጥታ ጋር በተያያዘ አዲስ መታወቂያ እንዳይሰጥ ጊዜያዊ እገዳ በመጣሉ በያዝነው ዕቅድ መሠረት የተቋቋሙ እናቶች መታወቂያ እንዲያገኙ ማድረግ አልተቻለም፡፡
- ከእገዳው በፍት በአዲስ አበባ ሴቶች፣ህጻናትና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ ድጋፍ እና በአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ለ275 ለሚሆኑ ከጎዳና ተነስተው ለተተቋቋሙ እናቶችና አዋቂዎች መታወቂያ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡
- በአሁኑ ወቅት እገዳው እየተነሳ ስለሆነ ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር እናቶች መታወቂያ እንዲያገኙ ስራዎች የሚሰሩ ይሆናል፡፡አፈጻጸሙም ውጤታማ እንዲሆን ተገቢው ክትትል ይደረጋል፡፡

# በክዋኔ ኦዲት የተሰጡ ማሻሻያ ሃሣቦች

3) ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከዓለም ባንክ የተገኘው ዕርዳታ ውሎና አዳራቸውን ጉዳና ላይ ላደረጉ የህብረተሰብ ክፍሎች የተመደበው የፋይናንስ መጠን ፤ለነማን እና በምን መስፈርት እንደተከፋፈለ በግልጽ የሚታወቅበት የአሠራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግና ምን ያህሉ ሥራ ላይ እንደዋለ የሚከታተልበትን አሠራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግና አፈጻጸሙን በተመለከተ ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት ሊያደርግ ይገባል፡፡

# በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተወሰዱ/በመወሰድ ላይ ያሉ የማስተካከያ እርምጃዎች

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከዓለም ባንክ የተገኘው የገንዘብ ድጋፍ በከተማ ልማታዊ ሴፍቲ-ኔት እና ስራ ፕሮግራም አካል የሆነው ውሎና አዳራቸውን ጉዳና ላይ ላደረጉ የህብረተሰብ ክፍሎች የተመደበው የፋይናንስ መጠን የሚያሳይ ከዓለም ባንክ፣ ፕሮገራሙን ከሚያስተባብረው ዩኒት(PCU) እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የተዘጋጀ ግልጽ የፕሮጀክት ማስፈጸሚያ መመሪያ(PIM) አለው፡፡ UPSNJP FINAL PIM.docx

የተዘጋጀውን የፕሮጀክት ማስፈጸሚያ መመሪያ(PIM )በአግባቡ እንዲፈፀም ሁሉም የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ አስፈጻሚ አካላት እንዲያውቁት በቂ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

ለዚሁ ስራ ማስፈጸሚያ የተመደበው ፋይናንስም አገልግሎት ላይ የሚውለው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ በሚወጣው ማስታወቂያ መሠረት አገልግሎቱን ለመስጠት ፍላጎታቸውን ለገለጹና በአፈፃፀም መመሪያ ላይ የተቀመጠውን መስፈርትን አሟልተው አገልግሎት ለመስጠት ያለፉትና ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ጋር የፕሮጀክት ስምምነት ውል ለገቡት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ነው፡፡

## ከላይ የቀጠለ------

የተመደበውም የፋይናንስ መጠን የሚወሰነው በፕሮጀክት ማስፈጸሚያ መመሪያ(PIM) ላይ በተቀመጠው መሠረት በጋዜጣ ላይ በወጣው የጨረታ ማስታወቂያ መሠረት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በሚያቀርቡት ፕሮፖዛል ላይ ዜጎችን ከጎደና ላይ አንስተው የተቋም አገልግሎት ለመስጠትና ለማቋቋም በሚያቀርቡት የተጠቃሚ ቁጥር ልክ (ለህጻን በወር 2065፣ ለአዋቂ በወር 2800፤ ለአረጋዊያን በወር 2205 እና አንድ ህጻን ለያዘች እናት ብር 2,800 ፣ሁለት ህጻናት ለያዘች እናት 3,800 ብር ሶስት ህጻናትን ለያዘች እናት ብር 4,800) በ18 ወር ተባዝቶ እንዲመደብ ይደረጋል፡፡ ይህም ተቋማቱ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ጋር በሚፈራረሙት የውል ሰነድ ላይ በግልጽ ተቀምጧል፡፡

# ከላይ የቀጠለ----

## የፕሮጀክቱን  አፈጻጸም ክትትል በተመለከተ በአፈጻጸም መመሪያዉ ላይ በተቀመጠው መሠረት፤

- አገልግሎት ሰጪ ተቋማትም የተመደበላቸውን ብር በአግባቡ ስለመጠቀማቸው በየ 3ወሩ  በሚያቀርቡት የፋይናነንስ አፈጻጸም ሪፖርት የሚገመገሚበት የአሰራር ስርዓት ተዘርግቷል፡፡
- የፋይናንስ ፍሠቱ ሙሉ በሙሉ የሚከናወነው በገንዘብ ሚኒስቴርና በተዋረድ ባሉት ተቋማቶቹ  ነው፡፡
- በየ ወሩ ማኔጅመንት ኮሚቴ ተሰብስቦ በፕሮጀክቱ አፈጻጸም ላይ ይወያያል፡፡
- ብሔራዊ አብይ  ኮሚቴ አባላቱ(የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳያ ሚንስቴር ሚንስተር፤ የከተማ ልማትና ኮንስራክሽን ሚንስቴር ሚንስተር እና የገንዘብ ሚንስቴር ሚንስተር)   በየ3 ወሩ እና እንደየአስፈላግነቱ በመገናኘት  ፕሮጀክቱን ይገመግማል ውሳኔዎችንም ያስተላልፋል፡፡
- በየ 6 ወሩ ዓለም ባንክ፤ ፕሮጀክቱን የሚያስተባብረው ዩኒት፤ ገንዘብ ሚኒስቴር ባሉበት የጋራ ክትትልና ግምገማ ይካሄዳል፤ በመጨረሻም ቀንም የግምገማ ወጤቱ ለከፍተኛ ሃላፍዎች(ሚኒስትሮች) ገለጻ ይደረጋል በቀጣይ ትኩረት ለሚሹ ጉዳዮችም አቅጣጫ እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡

4) ለእናቶች ከሕፃን ልጆቻቸው ጋር የተመደበው የገንዘብ መጠን የህክምናን ወጪ እና እናቶች ወደ ማዕከላቱ ይዘዋቸው የሚገቡ የሕፃናት ልጆችን ብዛት ከግንዛቤ ውስጥ ባስገባ መልኩ በየጊዜው ማስተካከያ የሚደረግበትን አሰራር ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

# በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተወሰዱ/በመወሰድ ላይ ያሉ የማስተካከያ እርምጃዎች

## የልጆችን ብዛት ከግንዛቤ ውስጥ በማስስገባት በሁለተኛው የፕሮጀክቱ ዙር (ከ2015 በጀት ዓመት) ጀምሮ በወር፡

- አንድ ህጻን ለያዘች እናት ብር 2,800 ፣
- ሁለት ህጻናት ለያዘች እናት 3,800 ብር
- ሶስት ህጻናትን ለያዘች እናት ብር 4,800 ሆኖ እንዲስተካከል ማሻሻያ ተደርጎበታል፤ ይህም በፕሮጄክቱ ማስፈፀሚያ ማኑዋል ላይ በግልጽ ተመላክቷል፡፡
- ለተገልጋዮች የሚመደበው የገንዘብ መጠንም በዓለም ባንክ አንድ ጊዜ በፕሮጄክቱ ስምምነት ጊዜ የሚፀድቅ በመሆኑ ለተገልጋዮች የሚሰጠው የገንዘብ መጠን የመግዛት አቅም በየጊዜው ብሔራዊ አብይ ኮሚቴ እየታየ ሌሎች በፕሮግራሙ የታቀፉት አገልግሎቶች ማሻሻያ ሲደረግባቸው አብሮ የሚታይ ሲሆን የዓለም ባንክ ይሁንታ ሲያገኝ ማሻሻያዎች የሚደረጉ እንደሆነ እንዲታወቅ፡፡

## በክዋኔ ኦዲት የተሰጡ ማሻሻያ ሃሣቦች

5) ሚኒስቴር መ/ቤቱ ውሎና አዳራቸውን ጎዳና ላይ ያደረጉ እድሜያቸው ለትምህርት የደረሰ ሕፃናት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ቀጣይነት ያለው መደበኛ ትምህርት እንዲያገኙ ለማድረግ ከክልሎችና ከከተማ አስተዳደሮች ጋር በመቀናጀት ሁኔታዎች መመቻቸታቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

# በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተወሰዱ/በመወሰድ ላይ ያሉ የማስተካከያ እርምጃዎች

- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከአገልግሎት ሰጪ ተቋማትና ከሚመለከታቸው የመንግስት ፈጻሚና አስፈጻሚ አካላት ጋር በጉዳዩ ላይ ምክክር አድርጓል ፡፡ ጉዳዩም አሳማኝ በመሆኑ በተለይ የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ከመንግስት የትምህርት ተቋማት ጋር በመነጋገር በርካታ ሕጻናት ወደ ትምህርት እንዲገቡ የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡ ይህም ቀጣይነት እንዲኖረው ተገቢው ክትትል የሚደረግ ይሆናል፡፡
- በተጨማሪም ወደ ቤተሰብ እንዲቀላቀሉ የተደረጉ ህጻናትም ወደ ት/ት ቤት እንዲሄዱ የማድረግ ስራዎች እየተሰራ ይገኛል፡፡

# በክዋኔ ኦዲት የተሰጡ ማሻሻያ ሃሣቦች

6) ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአገልግሎት ሰጪ ማዕከላት ለክልል /ከተማ መስተዳድር ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች በየ3 ወሩ የሚልኳቸው ሪፖርቶች ቢሮዎቹ በጋራ ሊገመግሙ፣በራሱ የሚያደርጋቸውንም የክትትል ፕሮግራሞችን መሰረት በማድረግ ግብረ-መልስ ሊሰጥና የግብረ-መልሶቹ ተግባራዊነትን ሊከታተል ይገባል፡፡

# በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተወሰዱ/በመወሰድ ላይ ያሉ የማስተካከያ እርምጃዎች

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በራሱ በሚያደርጋቸው የክትትልና ድጋፎች የሚያገኛቸውን ግኝቶች መሰረት በማድረግ ለአገልግሎት ሰጪ ተቋማትና ለአስፈጻሚ ተቋማት ግብረ-መልስ ሲሰጥ ቋይቷል፡፡ እንዲሁም በተሰጠው ግብረ መልስ መሠረት ችግሮቻቸውን መፍታት ያልቻሉ 11 የአገልግሎት ሰጪ ተቋማትም ላይ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ወስዷል፡፡
- በዚሁ መሠረት ሃላፊነት ያለባቸውና ፕሮጀክቱ በሚተገበርባቸው የሚገኙ ለክልል የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮዎች ተቋማቱ በየ3 ወሩ የሚልኳቸው የፈጻጸም ሪፖርቶችን በጋራ በመገምገም ግብረ-መልስ እንዲሰጣቸው ተደርጓል፡፡
- የተሰጡ ግብረ-መልሶችም ተግባራዊ ስለመደረጋቸው በድጋፋዊ ክትትልና ግምገማ ተረጋግጧል፡፡

# በክዋኔ ኦዲት የተሰጡ ማሻሻያ ሃሣቦች

7) ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፌዴራል መንግስት አስፈፃሚ መ/ቤቶች (እና ተጠሪ ተቋሞቻቸው) በወል ከተሰጣቸው ሥልጣንና ተግባራት አንዱ የሆነውን ለኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች የተጋለጡ የህብረተሰብ ክፍሎችን የሚያሳትፉ እና የሚጠቅሙ ተግባራትን በየተቋማቱ ከመደበኛ ሥራቸው ጋር አካተው (mainstream) እያከናወኑ መሆኑን የሚከታተልበትንና የሚያረጋግጥበትን ሥርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊነቱ የሚመራበትን አቅጣጫ የሚያሳይና ተጠያቂነትን የሚያሰፍን መመሪያ ወይም ጋይድላይን (mainstreaming guidline) ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡

# በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተወሰዱ/በመወሰድ ላይ ያሉ የማስተካከያ እርምጃዎች

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተሰጡ ማሻሻያ ሃሣቦች በመውሰድ ለኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች የተጋለጡ የህብረተሰብ ክፍሎችን የሚያሳትፉ እና የሚጠቅሙ ተግባራትን በየተቋማቱ ከመደበኛ ሥራቸው ጋር አካተው እያከናወኑ መሆናቸውን የሚከታተልበትንና የሚያረጋግጥበትን ሥርዓት እንዲሁም ተግባራዊነቱ የሚመራበትን አቅጣጫ የሚያሳይና ተጠያቂነትን የሚያሰፍን መመሪያ ወይም (mainstreaming guidline) ለማዘጋጀት በ2015 የበጀት እቅዱ ውስጥ በማካተት መመሪያውን ለመሰራት የሚያስችል የስራ መዝርዝር(ToR) አዘጋጅቷል፤ በቀጣይም ወደ ስራ የሚገባ ይሆናል፡፡

# ከላይ የቀጠለ---

- በተጨማሪም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች የተጋለጡ የህብረተሰብ ክፍሎችን የአካቶ ትግበራን የሚመራና የሚያስተባብር የአካቶ ትግበራ መሪ ሥራ አስፈጻሚ የሥራ ክፍል በማዋቀር ከ2015 የበጀት ጀምሮ ስራዎችን በማከናወን ላይ ነው፡፡
- ከጠ/ሚ/ር ጽ/ቤት ጋር በመተባበር ሚኒስቴር መ/ቤቱ እያንዳንዱ ተቋም(ተጠሪ ተቋማትም) ልጆች ወደ ጎዳና እንዳይመለሱ ከሜሪ ጆይ ጋር በመቀናጀት የመግባብያ ሰነድ ተፈራር**ሟል**፡፡child support

# የተሰጡ ማሻሻያ ሃሣቦች

8) ሚ/ር መ/ቤቱ ውሎና አዳራቸውን ጎዳና ላይ ያደረጉ ዜጎችን በተመለከተ ወቅታዊ መረጃዎችን ከሚመለከታቸው ከፌደራል ፣ከክልል እና እስከታችኛው አደረጃጀት ጀምሮ እንዲሁም መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር የሚለዋወጥበትን/ የሚሰበስብበትንና የሚደራጁበትን ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

# በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተወሰዱ/በመወሰድ ላይ ያሉ የማስተካከያ እርምጃዎች…

- በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከ2015 በጀት አመት ጀምሮ የማህበራዊ ጥበቃ የመረጃ አስተዳደርን የሚመራ ቡድን ተዋቅሮና ስራተኞች ተመድበውለት ማናቸውም ከመረጃ አስተዳደር ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን እንዲከታተልና እንዲመራ ተደርጓል፡፡
- ውሎና አዳራቸውን ጎዳና ላይ ያደረጉ ዜጎችን በተመለከተ ወቅታዊ መረጃዎችን ከሚመለከታቸው( ከፌደራል እስከታችኛው አደረጃጀት) ያሉ የመንግስት አስፈጻሚ አካላት እንዲሁም መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር የሚለዋወጥበት፤ የሚሰበስብበትና የሚደራጅበት ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት Urban Destitute Management Information System (udmis.gov.et) ለምቷል፡፡ በተጨማሪም:-
- Elderly Database Management Information System (edmis.gov.et)
- Social Protection Management Information System (www.spmistest.et)
- ለምተው ስራ ላይ ውለዋል፡፡ እነዚህንም Uniform Resource Locater (URL) ላይ ማግኘት ይቻላል፡፡

# የተሰጡ ማሻሻያ ሃሣቦች

9) ሚኒስቴር መ/ቤቱ  ከውጭ የሚገኙ እርዳታዎች ቀጣይነታቸው ላይኖራቸው ስለሚችል ውሎና አዳራቸው ጎዳና ላይ የሆኑ ዜጎችን ለማቋቋም ከአገር ውስጥ የፋይናንስ ምንጭ የሚደገፉበትን ሁኔታ በጥናት ጭምር በማስደገፍ ሥርዓቱ የሚዘረጋበትን ሁኔታ በማመቻቸትና አገር በቀል ተቋማት እንዲስፋፉ የሚደረግበትን ሁኔታ ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል ተቋማት ጋር በጋራ ሊሠራ ይገባል፡፡

# በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተወሰዱ/በመወሰድ ላይ ያሉ የማስተካከያ እርምጃዎች

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ውሎና አዳራቸው ጎዳና ላይ ያደረጉ ዜጎችን የማህበራዊ አገልግሎት በመስጠት እንዲቋቋሙ ለማድረግ ከውጪ በሚደረግ ድጋፍ ላይ የተንጠለጠለ ብቻ እንዳይሆን ከተለያዩ አካላት (በተለይ ከንግዱ ማህበረሰብ እና ከህብረተሰቡ) ሃብት ለማሰባሰብ የሚያስችል ብሔራዊ የማህበራዊ ጥበቃ ፈንድ መቋቋሚያ አዋጅ ጸድቆ ሥራ እንዲውል ለመንግስት አቅርቦ በመከታተል ላይ ነው፡፡በተጨማሪም በታችኛው የአስተዳደር እርከን የማህበረሰብ አቀፍ ጥምረት ህጋዊ በሆነ አግባብ በየቀበሌው ተቋቋመው ከማህበረሰቡ የተለያዩ ድጋፎችን (በዓይነትና በገንዘብ) በማሰባሰብ ዜጎች ወደ ጎዳና እንዳይወጡ ባሉበት አከባቢ ተገቢው ድጋፍ እየተደረገላቸው ይገኛል፡፡

# አመሰግናለሁ